# በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ተወላጆች

# በመኖርያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት የሚያስችል የአደረጃጀት አፈፃፀም መመሪያ

አዲስ አበባ

ጥር 1996 ዓ.ም.


የአ.አ.ከ.አ. የኅብረት ሥራ ማህበራት

ማስፋፊያ ጽ/ቤት

# በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንና የኢትዮጵያ ተወላጆችን በመኖርያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት የሚያስችል የአደረጃጀት አፈፃፀም መመሪያ

1. <u>የአባልነት መስፈርቶች</u>

   1.1 ዕድሜው ከ18 አመት በላይ የሆነ

   1.2 በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነ ሕጋዊ ተወካይ ማቅረብ የሚችል

   1.3 በአዋጅ ቁጥር 147/91 ድንጋጌ መሠረት የኅብረት ሥራ ዓላማዎችን መርሆዎችንና እሴቶችን ተቀብሎ ከሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው አመልካቾች ጋር በማህበር ተደራጅቶ ቤት ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ

   1.4 የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በሥራ ለመተርጐም ፈቃደኛ የሆነ

2. <u>አደረጃጀት</u>

   2.1 አባላቱ የሚደራጁት በኤንባሲያቸው አማካኝነት ይሆናል የአባላት ቁጥር ከአሥር በታች መሆን የለበትም

   2.2 የአዲስ አበባ ከተማ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት አስፈላጊውን የአደረጃጀት ሰነድ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚያቀርብ ይሆናል

   - የማመልከቻ ቅጽ
   - ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ
   - የአባላት ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ
   - የተወካዩች ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ
   - የምሥረታ ቃለ ጉባኤ ላይ ውይይት የሚደረግባቸውና ውሳኔ ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች

   2.3 ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከተደራጀ በኃላ በኤምባሲው በኩል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚላኩ ሰነዶች

   2.3.1 3 ኦርጂናል ቅጂ መተዳደሪያ ደንብ በተመረጡ ሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ

የተፈረመና የመስራች አባላት ዝርዝር፣ አድራሻና ፊርማ፣ የውሳኔ ስምምነት በስተጀርባው የተያያዘ፡-

2.3.2 የውክልና ማስረጃ ፎቶ ኮፒ /በሁለት ቅጂ/

2.3.3 የምሥረታ ቃለ ጉባኤ ይኸውም፣

- የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ የፀደቀበት፣
- የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓርማ ማህተም የተወሰነበት
- የሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ የተመረጡበት የአባላት ዝርዝር መረጃ
- የተወካዩች ዝርዝር መረጃ ያካተተ ሆኖ በሁለት አርጅናል ቅጽ ተዘጋጅቶ በተመሣሣይ ሁኔታ ይቀርባል

2.4 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የተላከለትን ሰነድ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተሙን በማሳረፍና በማረጋገጥ ማህበሩ ለመረጠው ያክፍለከተማ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ማደራጃ ቡድን በመሸኛ ደብዳቤ ይልካል በግልባጭም ለክትትል እንዲያመች ያለአባሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል::

2.5 የክፍለ ከተማው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቡድን ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በተላከለት ሰነድ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙትን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተወካዮች በመቀበል የራሳቸውን የሥራ አመራርና የቁጥጥር ኮሚቴ እንዲመርጡ ያደርጋል የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር፣ ሒሣብ ሹምና ገንዘብ ያዥ ይኖሩታል:: ሒሣቡን በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳሉ::

2.6 የክፍለከተማው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቡድን በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ዝግ ሆኖ የሚቆይና የቁጠባና ሒሣብ /Blocked Account / ተንቀሳቃሽ ሒሣብ /Current Acount/ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በመረጠው ባንክ እንዲከፈት ለባንኩ ደብዳቤ ይፅፋል የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በመረጡት የቦታ ስፋትና ሊዝ ተመን መሠረት እያንዳንዳቸው በነፍስ ወከፍ በማህበሩ ስም በተከፈተው ዝግ ሆኖ በሚቆይ ሒሣብ ውስጥ በየስማቸው ገቢ ያደርጋሉ:: በዝግ ሒሣብ እያንዳንዱ አባል የሚያስቀምጠው ገንዘብ መጠን

ሀ. እስከ 50 ሜ/ካሬ ቦታ አንድ ቤት ለሚሰራ ብር አራት ሺ

ለ. ከ51 - 250 ሜ/ካሬ ቦታ በላይ አንድ ቤት ለሚሰራ ብር ስምንት ሺ

ሐ. ከ251 ሜ/ካሬ ቦታ በላይ አንድ ቤት ለሚሰራ ብር አስራ አምስት ሺ ይሆናል

2.7 በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም የባንክ ሂሣብ ከተከፈተና የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ዝግ ሆኖ በሚቆየውና የተንቀሳቃሽ ሂሣብ ውስጥ በየስማቸው ገቢ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በኩል ሲቀርብ የክፍለከተማው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቡድን ለመሬት አስተዳደር የድጋፍ ደብዳቤ በመፃፍ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ተወካዬች አስፈላጊውን እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያግዛል በግልባጭም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሠረተ ልማትና የግንባታ ሥራዎች ባለስልጣንና ለአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት እንዲያውቁት ያደርጋል

2.8 ማህበሩ በመሬት አስተዳደር በኩል ቦታ ማግኘቱ እንደተረጋገጠ በክፍለ ከተማው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቡድን አማካኝነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከሁለት ቅጽ የመተዳደርያ ደንብና አንድ ቅጂ የምሥረታ ቃለ ጉባኤ ጋር ይሰጠዋል፣ የራስጌና የግርጌ ማህተም በተወካዬቹ አማካኝነት እንዲያስቀርፅ ይደረጋል፣ በተጨማሪም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስምና አድራሻ መሠረታዊ የሂሣብ ሰነዶችንና መዛግብቶችን በሟሟላት እንዲሁም ህጋዊ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመዘርጋት የሂሣብ እንቅስቃሴ ያደርጋል

2.9 ለአንድ የኅብረት ሥራ ማህበር የተወካዬች ዝቅተኛ ቁጥር 6 ሆኖ የሥራ አመራሩንና የቁጥጥር ኮሚቴውን የሥራ ድርሻ በመያዝ አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናሉ

2.10 ስለቦታ አሰጣጡም ሆነ ስለህንፃው ዲዛይን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ተወካዬች ከመሬት አስተዳደር ጋር በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት የሚፈፀም ይሆናል

2.11 የኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻና የሥራ ቦታ በማህበሩ በሚረከበው የግንባታ ቦታ ላይ ይሆናል

2.12 የኅብረት ሥራ ማህበሩ በተወካዬቹ አማካኝነት የግንባታ ሥራውን ከጀመረ በኋላ የተፈፀመውን የግንባታ ሥራ በመመዘን በማህበሩ ስም

2.13

በዝግ ሂሣብ የተቀመጠው ገንዘብ የሚለቀቀው በክፍለ ከተማው በመሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት አማካኝነት ይሆናል::

2.13 ይህ የአፈፃፀም መመርያ ተፈፃሚ የሚሆነው አዲስ ለሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲሆን ቀደም ሲል የተደራጁ ማህበራት የመተዳደርያ ደንባቸውን ብቻ በመቀየር መስተናገድ የሚችሉ ይሆናል

2.14 ሕጋዊ የመኖርያ ፈቃድ የሌላቸው አመልካቾች እውጭ አገር ስለመኖራቸው በኤምባሲዎቻቸው በኩል ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚቀርበው መረጃ መሠረት በተወካዮቻቸው አማካኝነት መደራጀት የሚችሉ ይሆናል

2.15 በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዩጵያዊያንና ኢትዩጵያውያን ተወላጆች በኤንባሲዎቻቸው በኩል በሚያቀርቡት የድጋፍ ደብዳቤና የነዋሪነት ማረጋገጫ መረጃ መሠረት በተወካያቸው አማካኝነት አገር ውስጥ ከሚኖሩ ኢትዩጵያውያን ጋር በመሆን በአንድ ማህበር መደራጀት የሚችሉ ሲሆን ቁጥራቸው ግን ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ከ1/3 መብለጥ አይኖርበትም::